## ማውጫ

ገጽ


1. መግቢያ ....................................................................................1

2. ማኅበሩ ሲቋቋም ይዞት የተነሳው ዓላማና ግብ.............................................3

3. ትኩረት የተደረገባቸው ሥራዎች ...........................................................4

4. የተከናወኑ ተግባራት ........................................................................5

4.1. ሕብረተሰቡን በአካባቢ ብክለት ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰሩ ሥራዎች.......5
4.2. ፓይለት ፕሮጀክት ስለማቋቋምና የሥራ እድል ስለመፍጠር ..............................9
4.3. የገንዘብና ቁሳቁስ ማስገኛ ስራዎች .......................................................10
4.4. የአባላትን ቁጥር ለመጨመር የተሰሩ ሥራዎች ..............................................12
4.5. የተለያዩ የፅዳት ዘመቻዎች ላይ የመሳተፍ ሥራዎች .....................................14

5. ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ አስከ አሁን ያስመዘገባቸው አንኳር አንኳር ውጤቶች .......................16

6. በማኅበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ..................................19

6.1. ቋሚ የሆነ ጽ/ቤት (ቢሮ) አለማግኘት ......................................................19
6.2. የገንዘብ አቅም ውሱንነት .........................................................................20
6.3. ለፕሮጀክት ማስፋፊያ የሚሆን ቦታ አለማግኘት.............................................20

7. ማጠቃለያ ...................................................................................22

## 1. መግቢያ

አዲስ አበባ የአገራችን ዋና ከተማ ከመሆኗ ባሻገር የብዙ ዲፕሎማቲክ ጽ/ቤቶች፣ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ አገር አቀፍ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች መናኻሪያ ከሆነች ረጅም ዓመታት አልፈዋል፡፡ ከተማዋ በአገር ውስጥና በውጪ ካላት ሰፊ ተቀባይነት አንፃር ዛሬ ከሚገመተው በላይ እየሰፋችና እያደገች ትገኛለች፡፡ ከከተማዋ መስፋፋት ባልተናነሰ ሁኔታ የሕዝቧ ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ግልጽ መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ በእርግጥ የከተማዋ ሁለንታዊ እድገትና መስፋፋት ለአንድ አገር ሥልጣኔና ብልፅግና አስፈላጊ መሆኑ ባይካድም አገሪቱ ካላት ማሕበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ተፈጥሮአዊ ይዘት ከተማዋ ያለተቀናቃኝ በብቸኝነት ይህን ሃብት መጠቀሟ ውሎ ሲያድር ችግር ማስከተሉ አልቀረም፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የሚመረቱት ምርቶች እንዲሁም ከመላው የዓለማችን ክፍሎች የሚመጡ ሸቀጣ ሸቀጦች ሁሉ የመጀመሪያ ማራገፊያ መሆኗ ሳያንስ  ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ገጠርና ከተማ ሳይል በሚደረገው የሰዎች ፍልሰት አማካይነት ከተማዋ ከሚገባው በላይ በሕዝብ ብዛት በመጨናነቅ ላይ ትገኛለች፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ መስፋፋት ከበጎ ገፅታው በላይ አሉታዊ ተፅእኖው እያስከተለ ያለው ችግር መጠነ ሠፊና ውስብስብ እየሆነ መምጣቱ ሳያንስ ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ ጭምር ምቹነቷን እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ ዛሬ ከተማችን ከእለት እለት ቁጥሩ እያሻቀበ በመጣው የመኪና ብዛት ተጨናንቃለች፤ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተቋማት በከተማዋ ቁጥራቸው እየጨመረ ነው፤ የነዋሪዎቿ ቁጥር እጅግ እያሻቀበ ነው፤ በከተማዋ የሚመነጨው የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ብቻ ሳይሆን አሉታዊ ተፅእኖው እየበረታ ነው፡፡ በእርግጥ በከተማዋ እየታዩ ያሉትን ሁለገብና የተያያዙ ችግሮች ዘርዝሮ መጨረስ ባይቻልም ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ግን በከተማዋ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ ዛሬ ከተማችን ከመኪናና ከፋብሪካ በሚወጡ በካይ ጋዞች (Smog) ተውጣለች፤ የነዋሪዎቿ ቁጥር ከከተማዋ ቅርፅና ስፋት ጋር ባለመመጣጠኑ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የተፋፈገ ኑሮ ከመኖራችን ባሻገር በዋና ዋና መንገዶቻችን ላይ እንኳን እንደልብ መንቀሳቀስ እየቸገረን ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ከከተማው ነዋሪ የሚወጣው ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ በዓይነትና በመጠን እየሰፋ መምጣቱ በጤናችን ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ መስፋቱ ሳያንስ ጥሩ ነገር የማየትና የማድነቅ ችሎታችንን እያደበዘዘው ይገኛል፡፡ የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላማ በከተማችን እየታዩ ያሉትን መጠነ ሠፊ የአካባቢ ችግሮች መዘርዘር ባይሆንም ማኅበራችን ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተፈጥሮን በማልማት ብክለትን ማስወገድ ማኅበር አሁን ወደተሰማራበት ሥራ ለምን እንደገባ መንደርደሪያ ሃሳብ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ዛሬ የከተማችንን ውበት እያደበዘዙና የነዋሪዎቿንና  የእንስሳትን እንዲሁም የእፅዋቶችን ጤና እየተፈታተኑ ከሚገኙ የከተማዋ ችግሮች መሀከል አንዱ የፌስታል ብክለት ችግር

ነው። ይህ ችግር የከተማችንን ውበት እያጠፋ ፣ የነዋሪዎቿን ጤና እያወከ ፣ የአፈር ለምነትን እያሳጣ፣ ከብቶችን እየገደለ እና ከጢስ ብክለት ጋር ተያይዞም በአጠቃላይ ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉት መንፈሳዊ ሰላሙ፣ እይታው፣ ጤናው …ወዘተ በማያስፈልጉ አካባቢያዊ የብክለት ተፅእኖዎች እየተዋጠ ይገኛል።

እነዚህንና የመሳሰሉትን የአካባቢ ብክለት ችግሮች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነበር ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተፈጥሮን በማልማት ብክለትን ማስወገድ ማኅበር በሚል ስያሜ በበጎ ፈቃደኛ ኢትዮጵያዊያት እናቶች ማኅበሩ የተመሰረተው። ማኅበሩ ይህንን ዓላማ አንግቦ በመጋቢት 15 ቀን 1996 ዓ.ም ከፍትሕ ሚኒስቴር ሕጋዊ ፈቃድ በማግኘት በአካባቢ ብክለት በተለይም በፌስታልና ጢስ ብክለት ዙሪያ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ወደ እንቅስቃሴ ገብቷል። ማኅበሩ ሥራ ሲጀምር በቂ የሆነ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅም ባይኖረውም፣በአባላት ዓመታዊ ክፍያ፣ በበጎ ፈቃደኛ ዜጎች መዋጮና ማበረታቻ እንዲሁም ከተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት በሚያገኘው ዕርዳታ አማካይነት ይህን የተቀደሰ አላማ ለማሳካት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። ይህም አጠር ያለ ሪፖርት ማኅበሩ ባለፉት ሦሥት አመታት ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት ይገልጻል።




*በከተማችን ተንሰራፍቶ የሚገኘው የፌስታል ብክለት ችግር*

## 2. ማኅበሩ ሲቋቋም ይዞት የተነሳው ዓላማና ግብ

ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተፈጥሮን በማልማት ብክለትን ማስወገድ ማኅበር ሲቋቋም የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በማቀድ ነበር።

1) የአዲስ አበባን ከተማ ለማፅዳትና የነዋሪዎቿን በተለይም የሕፃናትን ጤንነትና ኑሮ የተሻለ ለማድረግ፤
2) በየመንገዱ በልመና የሚተዳደሩ ወጣቶችና እናቶች በሥራ መስክ እንዲሰማሩ መርዳትና ማበረታታት ሕፃናቱም የሚጠበቁበትን ዘዴ ማመቻቸት
3) በማንኛውም የአዲስ አበባን አካባቢ ብክለት ለማስቀነስ በሚደረገው ጥረት ላይ መተባበር፤
4) የፅዳት ዘመቻዎች በማከናወን በተለይ በየመንገዱ ተጥለው የሚገኙትን ከፕላስቲክ የተሰሩ ከረጢቶችን (ፌስታል) እያስለቀሙ ቦታ ማስያዝና በሥራ (በጥቅም) ላይ የሚውሉበትን ዘዴዎች መፈለግ፤
5) ስለችግሩ ክብደትም ሆነ ስለሚወገድበት ዘዴዎች ጥናት በማካሄድ ከመንግስት፣መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሕብረተሰቡ ጋር በመመካከር ትብብራዊ ተግባራትን መፈፀም።

ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ማኅበሩ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

1) ጥናት ያካሂዳል፣ ሥልጠናና ጽሑፎችን እያዘጋጀ በመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ለሕዝብ በማድረስ ለማኅበሩ ዓላማዎች ግብ መምታት እንዲተባበሩ ያደርጋል።
2) የጽዳት ዘመቻ በማከናወን በተለይ በየመንገዱ ተጥለው የሚገኙትን ከፕላስቲክ የተሠሩ መያዣዎች (ፌስታል)እያስለቀሙ ቦታ ማስያዝና ሥራ ላይ ማዋል ወይንም በዘዴ እንዲወገዱ ያደርጋል።
3) ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ይረዳሉ ተብሎ ከታመነባቸው ማኅበሮች ከመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመለዋወጥ ይሠራል።

## 3. ትኩረት የተደረገባቸው ሥራዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎችና ግቦች ይዞ ነበር ማኅበሩ ወደሥራ የገባው። ስለዚህም ይህ ሪፖርት በነዚህ ትኩረት በተሰጣቸው ዓላማዎች አፈፃፀም እና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከመጋቢት ወር 1996 ዓ.ም ጀምሮ ያደረገውን እንቅስቃሴ አፈፃፀም ሪፖርት ባጭሩ ያስረዳል። የሪፖርቱ ይዘት ሰባት ክፍሎች ሲኖሩት ሪፖርቶቹም በተቻለ መጠን አጭርና ግልፅ እንዲሆኑ በማቀድ በሚከተለው መንገድ ተከፋፍለው ቀርበዋል ።

1. ሕብረተሠቡን በአካባቢ ብክለት በተለይም በፌስታልና ጢስ ብክለት ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰሩ ሥራዎች፤
2. ፓይለት ፕሮጀክት ስለማቋቋምና የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራዎች፤
3. የገንዘብና የቁሳቁስ አቅምን ለማጠናከር የተሠሩ ሥራዎች፤
4. የአባላት ቁጥርን ለማሳደግ የተሰሩ ስራዎች፤
5. በከተማዋ ውስጥ በተለያዩ ድርጅቶችና የሚመለከታቸው አካላት በሚያዘጋጁት የፅዳት ዘመቻዎች ላይ የመሳተፍ ስራዎች እና
6. በማኅበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች

# 4. የተከናወኑ ተግባራት

## 4.1. ሕብረተሰቡን በአካባቢ ብክለት ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰሩ ሥራዎች

በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ አምስት መሠረት ከማኅበሩ አላማዎች ውስጥ አንዱ በማናቸውም የአዲስ አበባን አካባቢ ብክለት ለማስቀነስ በሚደረገው ጥረት ላይ መተባበር ነው፡፡ በዚህም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሚሠሩት ሥራ ባሻገር ማኅበሩ ሕብረተሰቡን በአካባቢ ብክለት በተለይም በፌስታልና ጢስ ብክለት ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር የተለያዩ ጥረቶችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

ማኅበሩ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መሀከል አንዱ የሕብረተሰባችን በፌስታልና ጢስ ብክለት ዙሪያ ያለውን የተዛባ አመለካከት እንዲቀየር ማድረግ ሲሆን ይህንንም ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የውይይት መድረኮች፣ የቅስቀሳ እግር ጉዞ፣ ስልጠናና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ መድረኮች ላይ በመሳተፍ፣ በፅሑፍና በሚዲያ በመጠቀም የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር ሰፊ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ማኅበሩ ሲቋቋም አዘጋጅቶት በነበረው ስለማኅበሩ ዓላማና እቅድ እንዲሁም ስለፌስታል ብክለት በሚያትተው በራሪ ጽሁፍ (brochure) መግለጫ አውጥቷል፡፡ እንዲሁም በቅርቡ ማኅበሩ ከጥቅምት 11 — 19/1999 ዓ.ም አዘጋጅቶት በነበረው ታላቅ ጸረ የፌስታል ብክለት ዘመቻ ላይ የተለያዩ የፌስታልን ጎጂነት እንዲሁም መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የሚያንፀባርቁ በራሪ ፅሑፎችን (brochure) እና አንዳንድ የፅሑፍ መረጃዎችን ለሕብረተሰቡ በማሰራጨት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡





*ፕ/ር እንድርያስ እሸቴ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚደንት በጸረ ፌስታል ብክለት የእግር ጉዞ ላይ ንግግር ሲያደርጉ*

- ማኅበሩ ከጥቅምት 11-19 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የቆየ ታላቅ ጸረ የፌስታል ብክለት ዘመቻ በአዲስ አበባ ከተማ ባዘጋጀበት ወቅት ሦስት ዋና ዋና ፕሮግራሞችን ማለትም የውይይት መድረክ፣ የእግር ጉዞ እንዲሁም የፌስታል ለቀማ ውድድር በማዘጋጀት ሰፊ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በተለያዩ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ምሁራንን በመጋበዝ ለሕዝብ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡








*ከጥቅምት 11-19፣1999ዓ.ም በተዘጋጀው የጸረ ፌስታል ብክለት ዘመቻ ሳምንት የተካሄደው የውይይት መድረክ*

- ማኅበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ የፕሬስና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች የፌስታል ብክለትን በማስመልከት የተለያዩ ሥራዎችን ሰርቷል፡፡ በዚህም ከፕሬስ በሪፖርተር ጋዜጣ አማርኛ እና እንግሊዝኛ እትም፣ በአዲስ አድማስ፣ በ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም (United Nations

Environment Program) በራሪ ወረቀት ፣ በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማለትም በFM 97.1 ሬዲዮ በተለይም በደወል ፕሮግራም አማካይነት የተደጋገመ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅት እንዲቀርብ አድርጓል።በተጨማሪም በጀርመን ድምፅ ሬዲዮ( Radio DW) እና በመሳሰሉት ሌሎችም የሚዲያ ዘርፎች በፌስታል ብክለት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዜናዎች ፕሮግራሞች እንዲሁም ዘገባዎች እንዲቀርቡና ሕብረተሰቡም እንዲነጋገርባቸው አድርጓል። በዚህም በሰፊው ሕብረተሰብ ዘንድ በፌስታል እና ጢስ ብክለት ዙሪያ ያለው አመለካከት እንዲቀየር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

- ማኅበሩ የራሱን ድህረ ገፅ (Web site)* በመክፈት ስለዓላማውና ስለሚሰራቸው ስራዎች ያስተዋወቀ ሲሆን በዚህም የፌስታል እና የጢስ ብክለትን በተመለከተ ለአገር ውስጥና ለአለም አቀፉ ሕብረተሰብ ክፍት በማድረግ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል።
- ማኅበሩ የፌስታል እንዲሁም የጢስ ብክለትን በማስመልከት ከዚህም በላይ በአጠቃላይ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ዙሪያ አንዳንድ ጽሁፎችን በማዘጋጀት፣ ቃለ መጠይቆችን በማድረግ ለጋዜጦች እና መፅሄቶች እንዲላኩ በማድረግ ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሰርቷል።
- የማኅበሩ አባላት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ት/ቤቶችና የሙያ ማኅበራት በመሄድ ስለአካባቢ ብክለት በተለይም ስለፌስታልና ጢስ ብክለት ላይ ሰፋ ያለ ትምህርትና ሥልጠና ተሰጥቷል።




*የኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ዋና ሥራ አስኪያጅ በአየር አምባ ት/ቤት ስለ አካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ ትምህርት ሲሰጡ*

---

* የድህረ ገጹ አድራሻ www.sosaddis.org.et ነው።



*የኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተወካዮች ከአየር አምባ ት/ቤት ተማሪዎች እና መምህራን ጋር*

- ማኅበሩ በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ ት/ቤቶች ፣ ኮሌጆች፣ እንዲሁም የሙያ ማኅበራት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከመሥራቱም ባሻገር በተለይም በፀረ የፌስታል ብክለት ዘመቻው ላይ ተማሪዎች እና ማኅበራት የፌስታልን ጎጂነት እንዲገነዘቡ በማድረግ በፌስታል ለቀማው ውድድር እንዲሳተፉ የተጋበዙ ሲሆን በዚህም አበረታች የሆነ ውጤት ተገኝቷል፡፡
- ማኅበሩ ከነዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ወቅቶችና ቦታዎች በተዘጋጁ ስብሰባዎችና የውይይት መድረኮች ላይ በመሳተፍ የማኅበሩ አላማን እንዲሁም በፌስታልና በጪስ ብክለት ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ተሳትፎ አድርጓል ለምሳሌ የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፣ ፎረም ፎር ኢንቫይሮመንት ፣ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም እንዲሁም ሌሎች በአካባቢ ጥበቃ ላይ የተሠማሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የአካባቢ ጥበቃ ክበባት በተሳተፉበት ምድሪቱን እናፅዳ (Clean Up the World) ቀን ላይ ተሳትፎ በማድረግ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡
- ማህበሩ ዓለም አቀፍ የፅዳት ቀኖች ላይ በመሳተፍ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሕብረተሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ እንዳለበት ግንዛቤ በመፍጠር በተለይም ፌስታል በአካባቢ

ብክለት፣በሕብረተሰቡ እና በእንስሳት ጤና ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት በስፋት ገልፅዋል፡፡

- ለስራ ባቋቋመው የፓይለት ፕሮጀክት ለታቀፉ ሠራተኞች ተደጋጋሚ ሥልጠና የሰጠ ሲሆን በቀጣይም በተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ዙሪያ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡ በዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ ማኀበሩ ፌስታልን ሊተኩ በሚችሉ ሌሎች ምርቶች ዙሪያ ማለትም የጨርቅ፣ የወረቀት፣ የእፅዋት(ቀርከሃ፣ቃጫ) ወዘተ ምርቶች ሕብረተሰቡ እንዲጠቀምና የፌስታል ብክለት ጉዳት እንዲቀንስ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

## 4.2 ፓይለት ፕሮጀክት ስለማቋቋምና የሥራ እድል ስለመፍጠር

በማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ አምስት መሰረት ማኀበሩ አንግቦ ከተነሳባቸው ዓላማዎች አንዱ ስራ አጥ እና ችግረኛ ወገኖች በተለይም የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በልመና ተግባር የተሰማሩ ግለሰቦችና ሥራ አጥ ለሆኑ ወጣት ሴቶችና እናቶች ሰፊ የሥራ እድል በመክፈት ራሳቸውን ከመርዳት ባሻገር በአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በየካቲት ወር 1998 ዓ.ም በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 ውስጥ ማኀበሩ ፓይለት ፕሮጀክት በማቋቋም በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሥራ አጥ እናቶች፣ወጣት ሴቶች እና ወንዶች በፌስታል ለቀማ ሥራ ውስጥ በማሳተፍ አካባቢያቸውን ከፌስታል ብክለት እንዲታደጉ ከማድረጉም በላይ የገቢ ምንጭ በመፍጠር ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እንዲያስተዳድሩ አድርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ፡-

- ፓይለት ፕሮጀክቱ አላማው አድርጎ የተነሳው ሥራ አጥ ፤ ችግረኛ እንዲሁም በጎዳና ላይ ኑሮአቸውን እየገፉ የሚኖሩ እናቶችና ወጣት ሴቶች በሥራ መስክ ተሰማርተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በመርዳት አካባቢያቸውን ከብክለት እንዲታደጉ ማድረግ ሲሆን በዚህም ፕሮጀክቱ ሲጀመር የነበረው የሰራተኞች ቁጥር ከነበረበት 30 በመጨመር ዛሬ ቁጥሩ ከ80 በላይ ደርሷል፡፡ በዚህም ሰራተኞቹ የሰበሰቡትን ፌስታል ተረክቦ ፌስታልን እንደ ጥሬ እቃ በመጠቀም ሌሎች ምርቶችን ለሚያመርት ኢንዱስትሪ እያቀረበ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ የፅዳት ሰራተኛ በሚሰበስበው የፌስታል ኪሎ ግራም መጠን የሚከፈለው ስለሆነ ስራውን በቁርጠኝነት፣ ኃላፊነት በተሞላበትና በተሻለ ሁኔታ እንዲሰራ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡

- ሥራው ከተጀመረበት የካቲት 1998 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁም ድረስ ከ20,000 ኪሎ ግራም(14 ሚሊየን ፌስታል) በላይ ቆሻሻ ፌስታል ማኅበሩ የተረከበ ሲሆን በዚህም ሰራተኞቹ ከሚኖሩበት አካባቢ ባሻገር በሌሎች የከተማው ክፍል እየተንቀሳቀሱ ፌስታል እንደሚለቅሙና የገቢያቸው መጠን የሚለካው በሰበሰቡት የፌስታል መጠን ስለሆነ በርካታ ሰዎች ወደ ሥራው በመሳብ ያሉት የሰራተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሰበሰበውም የፌስታል መጠን እያደገ ይገኛል፡፡




*በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 በፓይለት ፕሮጀክት በፌስታል ለቀማ ሥራ የተደራጁ ሠራተኞች በሥራ ላይ*

- ማኅበሩ ከያዘው የአካባቢ ብክለት ችግርን የመቀነስ ሥራ በተጨማሪ በ4.1 ላይ እንደተጠቀሰው ሥራ ለፈጠረላቸው ወገኖች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት አከናውኗል፡፡ እንዲሁም በፓይለት ፕሮጀክት አካባቢ ለሚገኙ ወገኖች የሥራ ክቡርነት እና ተነሳሽነት መንፈስ እንዲኖራቸው በማድረግ የማኅበሩ ዓላማ ደጋፊዎች ሆነዋል፡፡

## 4.3 <u>የገንዘብና ቁሳቁስ ማስገኛ ስራዎች</u>

ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ማኅበር በበጎ ፈቃደኛና የአካባቢ መንሳቀል በሚያሳስባቸው ዜጎች እንደመቋቋሙ መጠን ቋሚ የሆነ የገንዘብ ምንጭና የቁሳቁስ አቅርቦት ስለሌለው በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የገንዘብ ማስገኛ (Fund Raising) ፕሮግራሞችን በልዩ ልዩ ቦታዎች በማዘጋጀት የገንዘብና የቁሳቁስ አቅሙን ለማሳደግ ሰፊ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም በአዲስ በረት በተዘጋጀው የቁርስ ግብዣ የገንዘብ ማሰባበቢያ ፕሮግራም ላይ ማኅበሩ የተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን ያከናወነ ሲሆን በዚህም በእለቱ ተጋብዘው ከመጡ እንግዶች ፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች እንዲሁም የአካባቢ መበከል ከሚያሳስባቸው ዜጎች የተወሰነ ገንዘብ ሊገኝ ችሏል።

- ማኅበሩ እንደ አንድ የገንዘብ ማግኛ ዘዴ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንዱ የማኅበሩን አባላትና ደጋፊዎች ቁጥር የመጨመር ሥራ ሲሆን በዚህም የክብር አባል፣ የቋሚ አባል፣ የተማሪ አባል እንዲሁም የህይወት ዘመን አባል በሚል ርዕስ በመከፋፈል ከነዚህ አባላት እንደየአቅማቸውና የሥራ ድርሻቸው አመታዊ ክፍያ በመሰብሰብ የድርጅቱን ገቢ ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል።
- በሌላ በኩል የማኅበሩ አባላት ግንዛቤ በማዳበር አባላቱ የሚቀርቧቸውን የማኅበሩን አላማ የሚደግፉ ሰዎች አባል እንዲሆኑ በማድረግ፤ ከዚህም በተጨማሪ አባላት ለግል ጉዳይ ወደ ውጪ አገር በሚሄዱበት ጊዜ እውጪ ከሚገኝ ዘመዳቸው ፣ ወዳጃቸው ወይም ቤተሰባቸው ጋር ስለማኅበሩ ሥራዎች አንዳንድ መረጃዎችን በመስጠት የገንዘብ እርዳታ የማሰባሰብ ሥራዎችን አጠናክረው እንዲሰሩ ተደርጓል።

- ማኅበሩ በሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች ላይ ፌስታልን የሚተኩ በማኅበሩ አባላት በእጅ የተሰሩ ከረጢቶችን በመሸጥ ፌስታልን ሊተኩ የሚችሉ አማራጮች እንዳሉ ከማሳየት በተጨማሪ ጥቂት ገቢ ለማግኘት ተሞክሯል።



*በማኅበሩ አባላት የሚሰሩት ፌስታልን ሊተኩ የሚችሉ ምርቶች ለእይታ በቀረቡበት ወቅት*

- ማኅበሩ ከአንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የፈጠረው ግንኙነት በማጠናከር የተለያዩ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ ያንን ያህል አመርቂ ባይሆንም የተወሰነ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ እንዲያደርጉ ጥረት ተደርጓል፡፡

- በተጨማሪ ማኅበሩ ባዘጋጀው ታላቅ ፀረ የፌስታል ብክለት ዘመቻ ወቅት በጎ ፈቃደኛ የሆነ ብቻ የሚገዛው ትኬት በማዘጋጀት ለማኅበሩ ገቢ ለማስገኘት ተሞክሯል፡፡

- ማኅበሩ በሚያደርጋቸው የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ላይ የተለያዩ ታዋቂ ሰዎችን በመጋበዝ የማኅበሩ ዓላማ ደጋፊ እንዲሆኑ በማድረግ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ለማስገኘት ተሞክሯል፡፡

## 4.4 <u>የአባላትን ቁጥር ለመጨመር የተሰሩ ሥራዎች</u>

የማኅበሩን አላማ ከግብ ለማድረስ የማኅበሩ አባላትን እና ደጋፊዎች ቁጥር እንዲጨምር  የተለያዩ ጥረቶችን ማድረግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሥራ እንደመሆኑ መጠን በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ ስድስት መሰረት  የአባላትን ቁጥር ለማሳደግ የሚከተሉትን ሥራዎች አከናውኗል፡፡

በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ ስድስት መሰረት በኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ውስጥ አባል ለመሆን

1. የማኅበሩ መስራች አባላትና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባኤ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል
2. ማንኛውን ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ እና የማኅበሩን ዓላማ በመቀበል መዋጮ ለመክፈል ወይም ለማኅበሩ የሙያ ወይም የጉልበት አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ ከሆነና ማኅበሩ በጠቅላላ ጉባኤው ያስቀመጠውን መስፈርቶች ካሟላ የማኅበሩ አባል ለመሆን ይችላል፡፡

- ማኅበሩ የራሱ የሆነ ቋሚ የገቢ ምንጭ የሌለው በመሆኑ  የአባላትን ቁጥር በማሳደግ የግንዛቤ ሥራ ከመስራት ባሻገር የአባላቱን ቁጥር በመጨመር የገቢ መጠኑን ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማኅበሩ የአባላቱን ቁጥር ለማሳደግ የሚከተሉትን  ሥራዎች አከናውኗል፡፡



*የኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ መስራች አባላት በከፊል*

- በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም በአዲስ በረት በተዘጋጀው የቁርስ ግብዣ ላይ የተገኙ እንግዶች የማኅበሩ አባል እንዲሆኑ በማድረግ የአባላቱ ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል፡፡

- ማኅበሩ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ሲያዘጋጅ እንዲሁም በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ሲሳተፍ ጎን ለጎን የአባላቱን ቁጥር ለመጨመር ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማኅበሩ አባላት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ውጪ አገር ሲንቀሳቀሱ ውጪ ለሚኖሩ ወገኖች እንዲሁም አላማውን የሚደግፉ ዜጎችን በማነጋገር የአባላት ቁጥር እንዲጨምር ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

- ማኅበሩ ባዘጋጀው ታላቅ የፀረ ፌስታል ብክለት ዘመቻ ፕሮግራሞች ውስጥ አንዱ በነበረው የውይይት መድረክ ወቅት ብዙ ሰዎችን አባል ማድረግ ተችሏል፡፡

- ማኅበሩ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋም ተማሪዎችን አባል ለማድረግ ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ከሚገኘውን የጂኦ ሶሳይቲ ኢንቫይሮመንታል ክለብ (Geo Society Environmental Club)

እንዲሁም በአራት ኪሎ ሳይንስ ፋኩሊቲ ከሚገኘውን የዋይልድ ላይፍ ሶሳይቲ (Wild life society) ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ፈጥሯል



*በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተባባሪ የጂኦ ሶሳይቲ ኢንቫይሮመንታል ክለብ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት*

- ማኅበሩ በሚሳተፍባቸው የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሁም ባገኛቸው የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ዕድሎች ላይ ማህበሩን በማስተዋወቅ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበሩ አባላት እንዲሆኑ ጥረት አድርጓል፡፡

- ከላይ በተጠቀሰው መልኩ በ20 ሰዎች አባልነት የተመሰረተው ማኅበሩ በአሁኑ ወቅት አንድ መቶ አስር (110) አባላትን ለማቀፍ ችሏል፡፡

## 4.5 <u>የተለያዩ የፅዳት ዘመቻዎች ላይ የመሳተፍ ሥራዎች</u>

ማኅበራችን ቆሻሻን በመሰብሰብ በተገቢው ቦታ የማስቀመጥ ተግባር የአንድ ወቅት ሥራ መሆን እንደሌለበት ያምናል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ወቅትንና ጊዜን ተንተርሰው በአንድ ሰሞን ሆይሆይታ ብቻ የሚሰሩ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ዘላቂነት ስለማይኖራቸው ቆሻሻን መሰብሰብ የአንድ ወቅት ሥራ ብቻ እንዳልሆነ ማኅበሩ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ለማስተማር ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- የማኅበሩ አባላት ከየመጡበት አካባቢ ለሚገኘው ሕዝብ ስለ ፌስታልና ጨስ ብክለት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በመስራት ሕብረተሰቡ በፌስታል ብክለት ዙሪያ ያለውን አመለካከት እንዲቀይር በማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴዎችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል የተወሰኑ አባላት በሚኖሩበት አካባቢ በየቦታው ተጥሎ የሚገኘውን ፌስታል አደገኛ መሆኑን በማስገንዘብ አንዳንድ አባላት ፌስታሉን በማስለቀም ሥራ ውስጥ ተሰማርተው ነበር፡፡

- የማኅበሩ አባላት የተለያዩ ተቋማት በተለያየ ጊዜያት በሚያዘጋጁት የፅዳት ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የፅዳት ሥራዎችን ከመስራታቸው ባሻገር አጋጣሚውን ተጠቅመው ስለ አካባቢ ብክለት በተለይም ስለ ፌስታልና ጨስ ብክለት የእውቀት ማስጨበጫ ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ ለምሳሌ ከመስከረም 16-18 ቀን 1999 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከበረው የምድሪቱን እናፅዳ (Clean up the World) ፕሮግራም ላይ የማኅበሩ አባላት በፅዳት ስራው ከመሰማራታቸው በተጨማሪ ስለ አካባቢ ብክለት በተለይም ስለ ፌስታልና ጢስ ብክለት አንዳንድ ግንዛቤዎችን በዕለቱ ለተሳተፉት አስጨብጠዋል፡፡

- ማኅበሩ ከጥቅምት 11-19 ቀን 1999 ዓ.ም "ፌስታል የክፍለ ዘመናችን ታላቅ የአካባቢ ስጋት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ከተማ ባዘጋጀው ታላቅ ፀረ የፌስታል ብክለት ዘመቻ ውስጥ አዘጋጅቶት በነበረው የፌስታል ለቀማ ውድድር የተለያዩ ማኅበራት፣ ት/ቤቶች እና ሰፊውን ሕብረተሠብ ያሳተፈ የፌስታል ለቀማ ሥራ ሰርቷል በዚህም በከተማችን የሚታየውን የፌስታል ብክለት ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ በአጋጣሚው ሠፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርቷል፡፡

- ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በፕሮጀክት ያሉትን ሠራተኞች በማንቀሳቀስ ቋሚ የሆነ በየወሩ የሚካሄድ የፅዳት ዘመቻ ፕሮግራም ዕቅድ አውጥቶ ወደ ተግባር ለመግባት ዝግጅቱን አጠቃሏል ፡፡

## 5. ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ አሰከ አሁን ያስመዘገባቸው አንኳር አንኳር ውጤቶች

ማኅበሩ ከተቋቋመበት ከመጋቢተ 1996ዓ.ም ጀምሮ አሁን የደረሰበት ደረጃ ለመድረስ የተለያዩ መሰናክሎች ያጋጠሙት ቢሆንም ከመንግስት ባገኘው ድጋፍ እና በበጎ ፈቃደኝነት በሚያገለግሉት አባላት ጥንካሬ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፡፡

- ማኅበሩ ከተመሰረተ ጀምሮ 20,000 ኪ.ግ(14ሚሊየን) ቆሻሻ ፌስታል ለማስለቀም ችሏል
- በማኅበሩ ስር ለተደራጁ ከ80 በላይ ለሚሆኑ ሥራ አጥ እናቶች፣ወጣት ሴቶች እና ወንዶች የሥራ ዕድል ፈጥሯል
- ከ 3,000 በላይ የማኅበሩን አላማ እና ከ5,000 በላይ ስለ ፌስታል ብክለት እና የመፍትሔ ሐሳቦች የሚገልፅ በራሪ ፅሁፎችን (Brochure) በማዘጋጀት ለሕብረተሰቡ አሰራጭቷል
- የአካባቢ ብክለት ችግር በተለይም የፌስታል እና የጭስ ብክለት ጉዳይ በሕብረተሰቡ፣ በመንግሥት እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድረጅቶች ትኩረት እንዲሰጠው የዘርፉ ምሁራንን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ከማኅበራዊ ጥናት መድረክ እና ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ኃላፊው ዶ/ር ኃይሉ ወርቁን ጨምሮ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ኃላፊ አቶ ሰይፉ ለገሰ እና ሌሎች የባለሥልጣኑን ባለሙያዎች እንዲሁም እንደ ፕ/ር እንድርያስ እሸቴ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት፣አርቲስት ስለሺ ደምሴ(ጋሽ አበራ ሞላ) የመሳሰሉ ታዋቂ ግለሰቦችን በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ በመጋበዝ የአካባቢ ብክለት ችግር ትኩረት እንዲያገኝ ጥረት ተደርጓል
- ማንኛውም የማኅበሩ አባልም ሆነ ግለሰብ ስለ ማኅበሩ ጠቅላላ ሁኔታ እና እንቅስቃሴ በቀላሉ መረጃ ያገኝ ዘንድ ማኅበሩ የራሱን ድህረ ገጽ ( Web site) ከፍቷል
- በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እና ማኅበሩ በሚያዘጋጃቸው ዝግጅቶች አማካይነት ከ150,000 በላይ ለሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል

- የአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ በተለይም የፌስታል ብክለት ችግር በሕብረተሰቡ ዘንድ ስርፆ እንዲገባ ከ 10 በላይ በሚሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በታተሙ የመንግሥት እና የግል ጋዜጦች ላይ የማኅበሩን እንቅስቃሴ እና የአካባቢ ብክለት ችግርን የሚገልፁ ፅሁፎች እንዲወጡ ተደርጓል

- በቀበሌ 01/02 አዲስ በተቋቋመው ፕሮጀክት 50 ለሚሆኑ ለሕብረት ፍሬ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ማኅበር አባላት ስለ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ፣ስለ ፌስታል ብክለት ችግርና መፍትሔዎቹ፣ስለ የግል እና አካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ እንዲሁም ስለ መጀመሪያ ደረጃ ሕክምና አስፈላጊነት የአንድ ቀን ትምሕርት ተሰጥቷል

- ማሕበሩ ወደ ፊት በት/ቤቶች፣በሴቶች እና ወጣት ማኅበራት ለሚያደርጋቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ይረዳ ዘንድ በአካባቢ ጥበቃ፣በፌስታል ብክለትና መፍትሔዎቹ፣በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ እና የመሳሳሉ ጉዳዮችን የሚያብራራ መመሪያ (manual) አዘጋጅቷል

- ማኅበራችን በፓይለት ፕሮጀክቱ የሚሰራውን የአካባቢ ጥበቃ እና የድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴ የጉብኝት ጊዜ በማዘጋጀት የአምባሳደሮች እና የዲፕሎማትክ ሚስቶች ማኅበር(Ambassadors and Heads of Mission Spouse Group) እና የአፍሪካ ሴቶች ዴቨሎፕመንት ፈንድ (African Women's Development Fund) ተወካዮች እንዲጎበኙ አድርጓል

- 5 የሚሆኑ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመሄድ ከ10,000 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተምሕርት ተሰጥቷል

- ከ500 በላይ ፌስታልን ሊተኩ የሚችሉ አማራጭ ምርቶችን አባላት እንዲሰሩ እና እንዲጠቀሙ በማድረግ ፌስታልን ሊተኩ የሚችሉ አማራጭ ምርቶችን ለሕብረተሰቡ አስተዋውቋል

- በ20 የአካባቢ ብክለት ተቆርቋሪ እናቶች የተመሰረተው ማኅበር ባከናወናቸው የተለያዩ ተግባራት አማካይነት ዛሬ የማኅበሩን ዓላማ የሚደግፉ ወደ 90 የሚጠጉ አባላትን ለማሰባሰብ ችሏል

- በተለያዩ የአካባቢ ብክለት እና ተዛማች ጉዳዮች ላይ በተጠሩ ከ50 በላይ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ጠቃሚ አስተያየቶችን ሰጥቷል

- የማኅበሩ ዓላማ ግብ ይመታ ዘንድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ከሚገኘው የጂኦ ሶሳይቲ ኢንቫይሮመንታል ክለብ (Geo Society Environmental Club) እና ሳይንስ ፋኩሊቲ ከሚገኙት ዋይልድ ላይፍ ሶሳይቲ (Wild Life Society) እንዲሁም ከጤና ቀበና እና ግንፍሌን እናጽዳ ማኅበር፣ከጽጌረዳ ባልትና እና ከመሣሰሉት ክበባት እና ማኅበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በቅርበት እየሰራ ይገኛል

- በጸረ የፌስታል ብክለት ዘመቻ ወቅት በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ከ1,000 በላይ የሚሆኑ የዩኒቨርስቲ፣ የኮሌጆች፣ የሁለተኛ እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እንዲሁም የተለያዩ ሲቪል ማኅበራት እንዲሳተፉ አድርጓል

- በጸረ ፌስታል ብክለት ዘመቻ ወቅት በተዘጋጀው የፌስታል ለቀማ ውድድር ከ350 ኪ.ግ (245,000) በላይ ቆሻሻ ፌስታል ከጎዳና ላይ እንዲለቀም አድርጓል

- በተመሳሳይ መልኩ በጸረ ፌስታል ብክት ዘመቻ ላይ 10ኪ.ሜ በሚሸፍነው ከምንሊክ አደባባይ በስድስት ኪሎ አድርጎ በቤተ መንግሥት በኩል መድረሻውን መስቀል አደባባይ ያደረገ የእግር ጉዞ በማዘጋጀት ከ2,000 በላይ የወጣት እና የሴቶች ማኅበራት እንዲሁም የዩኒቨርስቲ ፣የኮሌጆች፣ የአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን በማሳተፍ የፌስታል ብክለት ችግርን ለሕብረተሰቡ አስተምሯል፡፡

- በአዲሱ የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ እና አያዝዝ አዋጅ ላይ ማኅበራችን ባደረገው ከፍተኛ ጥረት መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት  ከ0.03 በላይ ውፍረት ያላቸው ስስ ፌስታሎች እንዳይመረቱ እና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ተደርጓል፡፡

## 6. ማኅበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች

ማኅበራችን ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ ለመድረስ መንገዶች ሁሉ ተደላድለው አልጠበቁትም። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ማኅበሩ በሙሉ እግሩ ከቆመበት ከመጋቢት 1996 ዓ.ም ወዲህ ለማኅበሩ እንቅስቃሴ በጎ አስተዋፅኦ ካበረከቱ ተግባራት ባሻገር የማኅበሩን እንቅስቃሴ በመግታት ወይም እንዲጓተት በማድረግ ማኅበራችን ሠፊ የሆኑ ችግሮችን አስተናግዷል። በማንኛውም ድርጅት እንቅስቃሴ ውስጥ ችግሮች መኖራቸው አያጠራጥርም። እንደማንኛውም ማኅበር (ድርጅት) ሁሉ ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስም ለአንዳንድ አላማዎቹ ግብ አለመምታት አስተዋፅኦ ያደረጉ መጠነኛና ከፍተኛ ችግሮች በ2005 እና በ2006 ውስጥ የተከሰቱ ሲሆን አንዳዶቹ እንደውም እስካሁንም ድረስ መፍትሄ ሳይገኝላቸው የተንጠለጠሉ መሆናቸው በማኅበሩ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተሉ ይገኛሉ። በእርግጥ በዚህ የሪፖርት ክፍል ማኅበሩ የገጠሙትን ችግሮች በሙሉ መዘርዘር ዓላማው ባይሆንም በማኅበሩ እንቅስቃሴ ውስጥ አሉታዊ ተፅእኖአቸውን በማሳረፍ ከፍተኛ እክል የፈጠሩትን ችግሮች ለመጠቆም ያህል ነው። በዚህም መሰረት ማኅበራችን በ2005 እና በ2006 የሚከተሉትን ዋና ዋና ችግሮችን አስተናግዷል፡-

1. ቋሚ የሆነ ጽ/ቤት (ቢሮ) አለማግኘት
2. የገንዘብ አቅም ውሱንነት
3. ለፕሮጀክት ማስፋፊያ የሚሆን ቦታ አለማግኘት

### 6.1. ቋሚ የሆነ ጽ/ቤት (ቢሮ) አለማግኘት

ማኅበሩ ሲመሰረት ይጠቀምባቸው የነበሩት ቢሮዎች ከልዩ ልዩ ደጋፊዎች ለምሳሌ ከወሴክማ፣ ከሪዲም ዘጄኔሬሽን፣ ወሴምኮ ወዘተ በማስፈቀድ ነበር ይሁንና የማኅበሩ እንቅስቃሴ እየሰፋና እየተጠናከረ በሚመጣበት ወቅት በበቂ ሁኔታ የተሟላ አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ፤ በተለያዩ ወቅቶች ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋሞች ሁሉ ማኅበሩ ቢሮ ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያከናውን ቆይቷል። በዚህም ከቀበሌ አንስቶ እስከ ከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን አካላት በደብዳቤ እንዲሁም በአካል በመቅረብ ማኅበሩ ቢሮ ለማግኘት ጥረት ቢያደርግም ጉዳዩ እስካሁን ድረስ መፍትሄ ሊያገኝ ካለመቻሉም በላይ በማኅበሩ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅእኖውን በማሳደር ሰፊ የሆነ ችግር እየፈጠረ ይገኛል።

## 6.2. የገንዘብ አቅም ውሱንነት

ከዚህ በፊት እንደተገለፀው ማኀበሩ ቋሚ የሆነ የገንዘብ ምንጭ ስለሌለው በአባላት መዋጮና አንዳንድ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች በተለያየ ወቅት በሚያደርጉት ልገሳ ላይ የተመረኮዘ የገቢ ስርዓትን ይዞ እንዲንቀሳቀስ ተገዷል፡፡ በግልፅ እንደሚታወቀው ማኀበሩ በመንግስት ደረጃ ለፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፤ ለአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎች አካላት የተሰጠውን የስራ ድርሻ ከመስራቱ ባሻገር ችግረኛ ዜጎች በስራ መስክ እንዲሳተፉ በማበረታታት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እንዲደግፉ ማድረጉ የታወቀ ሆኖ እያለ ከሚመለከታቸው የመንግስትና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ማኀበሩ የሚያከናውነውን እንቅስቃሴ ከግምት ውስጥ በማስገባት ያደረጉት የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑ የማኀበሩን እንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ካደረጉት ችግሮች መሀከል ሳይጠቀስ መታለፍ የማይገባው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ማኀበራችን የራሱን ፓይለት ፕሮጀክት አቋቁሞ ለአካባቢው ስራ አጥና ችግረኛ ዜጎች የገቢ ምንጭ እንዲፈጠር ቢያደርግም ማኀበሩ ከተነሳበት አላማና ግብ ጋር በተዛመደ መልኩ ከዚህ ስራ የሚያገኘው ትርፍ ገቢ የለውም፡፡ይሄም ሳያንስ ለፋብሪካ ከሚቀርበው አሮጌ ፌስታል ከሠራተኞች ክፍያ ውጪ የሚተርፈው ቀሪ ገቢ መልሶ ለፓይለት ፕሮጀክቱ ስራ ማስኬጃ ስለሚያውለው ማኀበሩ በቂ የሆነ ገንዘብ አለማግኘቱ የተለያዩ ጠቃሚ ሥራዎችን እንዳያከናውን አስገድዶታል፡፡

## 6.3. ለፕሮጀክት ማስፋፊያ የሚሆን ቦታ አለማግኘት

ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ በ1998ዓ.ም የ74 ሚሊየን ብር ፕሮጀክት አዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ ኦክስፎርድ ፖሊቴሊን ከሚባል የፕላስቲክ አምራች ድርጅት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ውስጥ አንድ ሰፊ የሆነ የመልሶ ጥቅም ኢንዱስትሪ (Recycling Industry) በመክፈት ለ25,000 የሚሆኑ ስራ አጥ ወገኖች የስራ እድል እንዲያገኙና በአጋጣሚውም የአገራችንን ተረፈ ምርት በመቀነስ ወደ ሌሎች ምርቶች በመቀየርና ገቢ ለመፍጠር ነበር፡፡ ይሁን እና ለፋብሪካው ማቋቋሚያ የሚሆን መሬት በተጠቀሰው ክ/ከተማ ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ሊሳኩ አልቻሉም፡፡ በእርግጥ ይሄ ሃሳብ መንግስት አሁን ከያዘው የድህነት ቅነሳና ሰፊ የስራ እድል መፍጠር ስትራቴጂ አንፃር ተቀባይነቱ ባያጠራጥርም ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ግን ይህ ነው የሚባል አጥጋቢ መልስ ማኀበሩ ሊያገኝ አልቻለም ማኀበሩ ይህንን አላማውን ከግብ ለማድረስ አሁንም ጥረቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ማኀበሩ ይዞት የተነሳውን የፌስታል ብክለት ችግርን የመቅረፍ አጀንዳ ለማሳካት ሕብረተሰቡን ስለችግሩ አስከፊነት ከማስተማር ጎንለጎን ፌስታልን ሊተኩ የሚችሉ እና አካባቢን የማይበክሉ አማራጭ ምርቶች በማምረት ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ

ለድርጅቱ ሥራ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ባያጠራጥርም ከላይ በተጠቀሰው የቦታ ማጣት ችግር ምክንያት ይህን ሥራ ማከናወን አልተቻለም፡፡ እንዲሁም በማህበሩ ስራ ውስጥ ለሚሳተፉት የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ ጊዜ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ሥልጠናውን ለማካሄድ የሚያስችል የቦታ (የአዳራሽ) አለመኖር ሥልጠናው እንዳይከናወን ትልቅ መሠናከል ፈጥሯል፡፡

## 7. ማጠቃለያ

ከላይ ከክፍል 1 እስከ 6 በከተማችንና በአገራችን ባጠቃላይ ያለው የአካባቢ ብክለት ችግር ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ መሆኑ በስፋት ተገልጻል፡፡ ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስም ይህን የአካባቢ ብክለት ችግር ለመከላከል አቅም በፈቀደ መጠን የራሱን በጎ አስተዋፅኦ በማበርከት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከላይ በቁጥር አምስት በስፋት እንደተገለፀው ማኅበሩ እስከ አሁን ያከናወናቸው ተግባራት ካለው ሰፊ የአካባቢ ብክለት ችግር አንፃር እንደ ጀማሪ ድርጅት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ወደ ፊትም ከዚህ በበለጠ መልኩ ያጋጠሙትን ችግሮች በመፍታት በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያንዣበበውን የብክለት አደጋ ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

የአካባቢ ብክለት ችግርን ለመከላከል ከሚደረጉት ተግባራዊ ሥራዎች በተጨማሪ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አስፈላጊ በመሆኑ ከተግባር ሥራው ጎን ለጎን ተጠናክሮ እንዲቀጥል በአዲሱ የበጀት አመት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፌስታልም ሆነ ሌሎች የአካባቢ ብክለት ችግሮች በዘላቂነት ለመቅረፍ ከምንጫቸው ማድረቅ አስፈላጊ በመሆኑ አካባቢን የሚበክሉ ምርቶች እንዳይመረቱና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ከመከላከል በተጨማሪ የሕብረተሰቡን ልምድ እና እውቀት (indigenous knowledge) በመጠቀም አካባቢን ሊበክሉ የማይችሉ(Environmental Friendly) ምርቶችን በማምረት ለሕብረተሰቡ በማስተዋወቅ የአካባቢ ብክለት ችግርን ለማስወገድ ከመቼውም የበለጠ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

በአዲሱ የበጀት ዓመት ይህ እየተከናወነ ያለውን የአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ ከሥራ አጥነት (ድህነት ቅነሳ) ጋር በይበልጥ በማስተሳሰር ቁጥራቸው በርከት ያሉ በዝቅተኛ የኑሮ ጀረጃ ላይ የሚገኙ እናቶች ፣ ሴቶች እና ወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

በመጨሻም ማኅበራችን የሚያከናውናቸውን ሥራዎች በሥፋት በማስተዋወቅ ያሉበትን ችግሮች ከመንግሥት ፣ ከሕብረተሰቡ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከማኅበራችን አባላት ጋር በመተባበር ለመቅረፍ እነዚህ አካላት ከዚህ በፊት ያደርጉት የነበረውን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጽኑ እምነታችን ነው፡፡